# የትግላችን መዳከም ፤ የወያኔ መጠናከር

ከመይሳው

ወያኔ በምርጫ 97 ከኢትዮጵያ ሕዝብ በደረሰበት ከፍተኛ ቡጢ ተደናግጠ ግብዓተ መሬቱ እንደተቃረበ በመገንዘብና በመርበድበድ ክፉኛ የተቅበዘበዘበት የወቅቱ እውነታ ነበር ፤ ስለሆነም ጠ/ሚኒስትሩም ለአስራ አራት ዓመት በሕዝቡ ላይ ያደረሰውን በደልና ግድያ ያውቅ ሰለነበር ክፉኛ በተቆጣው ሕዝባዊ አመጽ ሊደርስበት የሚችለውን አይቀጡ ቅጣት አስቀድሞ ስለተገነዘበ የውድቀቱን አይቀሬነት በማመን ፍርሃቱ አይሎበት አገር ጥሎ ለመፈርጠጥ አኮብኩቦ ለኢትዮጵያ የአየር ኃይል የተጠንቀቅ ትእዛዝ በመስጠት ግርግሩና አመጹን ለማፈን የመጨረሻ ጭካኔ የተሞላበት ግድያና አፈና በመጠቀም ሊወጣው ከቻለ እሰየው ካልሆነም ከደሃው የኢትዮጵያ ሕዝብ የዘረፈውን መጠን የለሽ ገንዘብ ተሸክሞ ወደ ባእድ ሐገር ለመኮብለልና ለመፈርጠጥ ያመቸው ዘንድ አዳሩን ደብረዘይት በሚገኘው የአየር ኃይል አድርጎ እንደነበር ሁላችንም የምናውቀውና የቅርብ ጊዜ እውነታና ያደባባይ ሚስጥርም የነበረ የምናውቀውም ሃቅ ነው፤፤

ይህ ሁሉ አርድ አንቀጥቅጥ የሆነው የሕዝብ አመጽ በግፈኛው የወያኔ የዘር አገዛዝ ላይ ታላቅ ድንጋጤና መርበትበትን ያስከተለው የድርጅቶች የጋራ ጠላታቸውን በማወቅ ከስር መሰረቱ ገርስሦ ለመጣል በአንድነትና በተቀናጀ መንገድ መስራታቸው ብሎም ሕዝቡ “ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ” ያለው ቃል ስለተከበረለት ሳያወላዳ ያልተቆጠበ ድጋፉን በመስጠቱ እንደነብረ እውን ነው፤፤ የዚህ አይነቱ ሕብረትና አንድነትም በሐገር ቤት ብቻ የተወሰነም አልነበረም በሐገር ቤቱ የነበረው ሕብረትና አንድነት በተመሳሳይ መልኩ በሰሜን አሜሪካ ፤ በአውሮፓ ፤ በመካከለኛው ምስራቅና በአፍሪካም በሚገኙት ኢትዮጵያውያን ላይ በከፍተኛ ስሜት ሲንጸባረቅ ታይቷል ፤፤ ሆኖም ግን የወያኔው ዘረኛ መንግስት እየተንገዳገደም ቢሆን ሕዝቡን በጭካኔ በመጨፍጨፉና የተቃዋሚ መሪዎችንና ከ40 ሺህ በላይ የሚሆኑ ደጋፊዎቻቸውን ወደ እስር ቤት በመወርወሩና በማጎሩ ምክንያት በሐገርቤት ትግሉ ከነበረው ፈጣን እርምጃ በመጠኑም ቢሆን ሊገታው ችሏል ሆኖም ግን በውጪ የሚገኘውን የተቃዋሚ ደጋፊውችን የሚቆጣተርበት ምንም አይነት (mechanism) ስላልነበረው በውጪው ዓልም ያለው ኢትዮጵያዊና ሕዝባዊ ወገን ትግሉን በማቀጣጠል ወያኔን እስትንፋስ ባሳጣ ሁኔታ ይጓዝ ስለነበር የዘረኛው መንግስት በሐገር ቤቱ ለጊዜው ትንፋሹን መዋጥ ቢችልም እንኳን የውጪው ትግል በተቀላጠፈ መንገድ ወያኔን በማጋለጥ ያላሳለሰ ተጋድሎውን በመግፋቱ የውጪው ትግል የእግር እሳት ሆኖበት የሚይዝ የሚጨብጠውን ያጣበት ፤ እንደ እብድ ውሻ የተቅበዘበዘብት ወቅት እንደነበረ የምናስታውሰው የትላንት ትዝታችን ነው፤፤

ታዲያ ይህ ሁሉ ጥረትና ድካም ዛሬ በኢትዮጵያዊው መሀክል የማይታየው ከምን የተነሳ ነው? ለማስታወስ ያክል የወያኔው ዘረኛ መንግስት ትግሉን ለመግታት ያስቻለው ዘንድ ብሎም በውጪ ያለውን የተቃዋሚ ቡድን ለመከፋፈል መርዘኛና በታኝ የሆነ ረቂቅ በማውጣትና ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ወጪ ለዚሁ የመከፋፈያ ተግባር በመመደብ “ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፓብሊክ ኤምባሲ ቋሚ መልእተኛ ጽ/ቤት ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት በያሉበት” በሚል ርእስ በመላው ዓለም ለሚገኙት ኢምባሲዎቹ ያሰራጨው የመከፋፈያ መመሪያና መርሀ ተግባራዊነቱ ግቡን የመታ ይመስላል ፤ ይህም ማለት ምን ያክል የላላና መሰረት የሌለው አንድነት እንደነበረ ያለን ይጠቁማል ፤ በተጨማሪም የ (AFD እና Kil) መመስረት በነበረው ሕብረትና ትግል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ እንደቸለሰበት እሙን ነው ፤ የ AFD ምስረታ በሻቢያ አቀነባባሪነት የተመሰረተና ፤ ኢትዮጵያን በዘርና በጎጥ ለመበታተን የተቀነቀነ እንደሆነ ፤ ለኢትዮጵያ ሉአላዊነት ደንታ የሌለው አልፎ ተርፎም በመላው ኢትዮጵያዊ የተመረጠውን ዘረኝነትና ግንጠላን አጥበቆ የሚቃወመውን ቅንጅትን የሚያንኳሥሥና የበላይነቱን ኢትዮጵያዊነቱን ለማይቀበልና ኢትዮጵያን ለመበተን ደፋ

ቀና ለሚል ኦነግ ለተባለ ዘረኛና አፍራሽ ድርጅት እጅና እግሩን አስሮ በመስጠቱ ፣ ፀረ ኢትዮጵያ የሆነ ሰነድ በመፈራረሙ ፣ ተገንጣይና የሻቢያ ቡችሎች የሆኑ መሰል የተገንጣይ ቡድኖችን በማሰባሰብና የት ነበሩ የማይባሉ የብተና ቡድኖችን እውቅና በቅንጅት ስም በማስገኘቱ ፣ ለሐገራችን የበለጠ መከራ በመጋበዙ ፣ ኢትዮጵያዊ አቋም ያላቸውን ድርጅቶች ሕብረት (UEDF)ን በማግለልና አብሮም ለመስራት ፈቃደኛነትን ባለማሳየቱ ፣ እነዚህንና የመሳሰሉ ደንቃራዎች በትግሉ ላይ በመከሰታቸው የቀሰለ ጥንቸል የነበረው ወያኔ ዛሬ እድሜ ለ AFD እና በኢትዮጵያ ስም ለሚነግዱ በ (Diaspora) ላሉ ሁለት ቅንጅት ነን ባዮች ወያኔ ዛሬ የነበረበት ፍርሃት ቀርቶ ደረቱን ነፍቶ እንደ አንበሳ ማጋሳት ከጀመረ ውሎ አድሯል ፣ በመሆኑም ለጸረ ወያኔ ትግል በገንዘቡ ፣ በጉልበቱ ፣ በእውቀቱ ያልተቋረጠ አስተዋፆ ያደርግ የነበረው ብዙሀኑ ኢትዮጵያዊ ተስፋ እንዲቆርጥና ከትግሉም እንዲሸሸ እነኚህ በኢትዮጵያዊነትና በአንድነት ስም እየሰበኩና እየማሉ የወያኔን ተልእኮ የሚያራምዱ ተመፃዳቂዎች ዛሬ ትግሉ ለደረሰበት አሳዛኝ ሁኔታ ታላቅ አስተዋፆ እያበረከቱ ለመሆናቸው አያጠያይቅም ፣ ለወያኔ መጠናከርና ለምናደርገው ጸረ ወያኔ ትግል መዳከም ከወያኔም ይሁን ከሌላ በሚያገኙት እርዳታ ታላቅ አስተዋጽፆ በማበርከት ድርሻቸውን ተወጥተዋል ፣ ባላቸው ስውርና ግላዊ አጀንዳ ለወያኔ ጉልበት ለተቃዋሚው ድክመት ሆነው ትግሉ ወደፊት እንዳይራመድ እንቅፋት በመሆን ታላቅ አስተዋጽፆ አበርክተዋል ፣ ባላቸው የሬድዮ ፣ የድሕረ ገጽ ፣ በዘመን አመጣሹ (pal talk) በመባል በሚታወቀው የማጥቃት ዘመቻና (misinformation) ክፍሎች ጸረ አንድነትና ጸረ ሕብረት የሆኑ ካድሬዎቻቸውን በማሰማራት ከፍተኛ የሆነ ውዥንብር በመፍጠራቸው የሕብረቱንም (UEDF)ን ስም ባላቸው ኃይል በአናሳ ካድሬዎቻቸው አማካኝነት ቀን ከሌት በሌለና በማይመስል የስም ማጥፋት ዘመቻ በመኮርኮም ሕብረቱም ያለውን ኃይል አሰባስቦ ጸረ ወያኔ ትግሉን እንዳያካሂድ የዋህ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በማወናበድ ለሕብረቱ ድጋፍ እንዳይሰጡ ታላቅ እንቅፋት በመሆን ለወያኔ አሌ የማይባል አስተዋጸኦ በማድረጋቸው ትግሉ ቅጡን እንዲያጣና ወያኔ እንዲጠናከር ግንባር ቀደም በመሆን ከፍተኛ ድርሻቸውን እየተወጡ መሆናቸው ይታወቃል ፣ ይኸው ዛሬ ወያኔ ክምን ጊዜውም በላይ በመጠናከር (Ethiopians forum for political civility) የሚባል የ (pal talk )ክፍል በመክፈት ከዚህ ቀደም ወያኔን ደግፎ መናገር ይቅርና ወያኔን ደግፈው በጽሁፍ ሃሳባቸውን መግለጽ ይፈሩ የነበሩት ወያኔዎች ሁሉ ዛሬ አለምንም ፍርሀትና ሀፍረት ቅንጅትን ሲያንጓጥጡና በትግላችን ሲዘባበቱ መስማት የዘወትር ተግባራችን ሆኗል ፣ አልፎ ተርፎም የወያኔ ባለስልጣናትንና ከዳተኛው ልደቱን እክፍላቸው ድረስ በመጋበዝ የተለመደ ወያኔያዊ መርዛቸውን በመርጨትና በመከፋፈል ከፍተኛ የሆነ ጸረ እትዮጵያዊነት እየተሰተጋባ እንደሆነ እየተገነዘብን ነው ፤፤ እንግዲህ ወያኔ ያለውን ኃይል ከአገርቤት አውጥቶ እዚህ (Diaspora) ድረስ በማስገባት በከፍተኛ ፍጥነት እየተጓዘ መሆኑን እያስመሰከረ ነው ፤፤ ታዲያ የኛዎቹ ተቃዋሚ ተብዬዎች ይህንን ሁሉ እያዩ ዛሬም አልተሳሳትንም ካፈርኩ አይመልሰኝ እያሉ ውድ ሐገራችንን አይወድቁ አወዳደቅ እየወደቀች አንዱ አንዱን እየኩነኑ ከጸረ ኢትዮጵያ ድርጅቶች ከሚለየኝ ከኢትዮጵያ ይለየኝ ማለታቸው የሚሰሩት ለሕዝብና ለኢትዮጵያ መሆኑ አጠያያቂ ይሆናል ፣ በመሆኑም በኢትዮጵያዊነቱ የሚቆጭና የሚንገበገብ ሁሉ የነኚህን በኢትዮጵያዊነት ስም የሚምሉትን ቀረብ ብሎ መመርመርና አካሄዳቸውን በሐገር ቤት ለሚገኘውም ወገናችንም ሆነ በ (Diaspora) ለሚገኘው ኢትዮጵያዊ በማያሻማ ሁኔታ አካሄዳቸውን በማጋለጥ የተዳከመውን ትግላችንን ቀድሞ ወደነበረው አንድነትና ሕብረት ይመጣ ዘንድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ድርጅቶችና ኢትዮጵያዊው ሁሉ ትግሉን የማፋፋምና የማጠናከር ኃላፊነት እንዳለበት ተገንዝቦ ለነገ ይደር የማይባል እንገብጋቢ የሐገር ጉዳይ እንደሆነ በማመንና በመገንዘብ ትግሉን እንደቀድሞው እንድናፋፊም ለመላው ኢትዮጵያዊ ድርጅትና ሐገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ስለ ኢትዮጵያ አንድነትና ልእልና ሲባል የትግልና የአንድነት ጥሪዬን አስተላልፋለሁ ፤፤

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል!!**